## ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)፣
## ከሰማያዊ ፓርቲ (ሰማያዊ)
## እና
## ከኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጐ (ሸንጐ)
## የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

# አገራችን ውስጥ የሚታየውን ቀውስ ለማርገብ መፍትሄው ከቃላት ያለፈ ተጨባጭ እርምጃ መውሰድ ብቻ ነው!!!

ኢህአዴግ አሁን እየታየ ያለው የአገሪቱ አሳሳቢ ሁኔታ ባሳደረበት ብርቱ ተፅዕኖ ታኅሣሥ 25 ቀን 2010 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋትና ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር ያስችላል በሚል የፖለቲካ እስረኞችን እንደሚፈታና በወታደራዊ ደርግም ሆነ በራሱ የኢህአዴግ መራሹ አገዛዝ ማዕከላዊ በተሰኘው የሰቆቃ እስር ቤት ግፍ ሲፈፅምበት የኖረውን ሥፍራ እንደሚዘጋና ወደ ቤተ መዘክርነት እንደሚቀይረው አውግቷል፡፡

ይህ አፋኝና አምባገነን አገዛዝ ላፉት 26 ዓመታት በጠመንጃ አፈሙዝ ሕዝብን እየገዛና ለዲሞክራሲ ልዕልና የሚታገሉ ወጣትና አንጋፋ ፖለቲከኞችን፣ ጋዜጠኞችን እና ንፁሀን ዜጐችን በጅምላ ለእስር እየዳረገ ማሰቃየቱን ዓለም የሚያውቀው ነው፡፡

የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር ተቃዋሚዎች እግር ሲያወጡ እየተከታተሉ እንደሚቆርጡ የተናገሩትን አባባል ተግባራዊ በማድረግ ለተቃውሞ አደባባይ የሚወጡ ዜጐችና የፓርቲ መሪዎችን ለእስር በመዳረግ እነሆ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ኢህአዴግ አገሪቱ መስቀለኛ መንገድ ላይ ባለችበት ወቅት የፖለቲካ እስረኞች መኖራቸውን ማመኑና ለመፍታት ቃል መግባቱ ደበል የሚያሰኝ ቢሆንም፤ አገዛዙ ሊታመን የሚችለው የገባውን ቃል ተግባራዊ ሲያደርግ ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ኢህአዴግ እስረኞች ይፈታሉ፡፡ ማዕከላዊም ይዘጋል ብሎ በተናገረ በቀናት ልዩነት ይህንኑ አቋሙን በተደጋጋሚ እንደቀያየረና ውስን እስረኞችን እንደፈታ በሬዲዮና በቴሌቪዥን መግለጫ ቢሰጥም እስረኞችን ለመፍታት መስፈርት ማስቀመጡ ሲታይ የአገዛዙ ሰለባ የሆኑ ታሳሪዎችን በሙሉ ላለመፍታት እያቅማማ ስለመሆኑ አመላካች ነው፡፡

በተለይ የፀረ ሽብር ህጉን ተገን አድርጐ ሰላማዊ ዜጐችን አርበኞች ግንቦት 7፣ ኦነግ፣ ኦብነግ፣...ወዘተ የሚል ታፔላ እየለጠፈ በግፍ ያሰራቸውን የአገሪቱን የቁርጥ ቀን ልጆች ሳይፈታ፤ ስለብሔራዊ መግባባት ማውሳቱ ሚዛን የሚደፋ አይደለም፡፡

[illegible] ነው::

በሀገራችን ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች እንደሚገኙ ይታወቃል:: የታሰሩትም አመለካከታቸው ከገዥው ቡድን ጋር ባለመጣጣሙና አገዛዙ “በጠላትነት” ስለፈረጃቸው ነው፡፡ ስለሆነም የፖለቲካ እስረኞችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፍታት ሀገሪቱም አሁን ካለችበት ሁለንተናዊ አጣብቂኝ በማውጣትና ተቀራርቦ በመወያየት ረገድ የሚያግዝ መሆኑ በቅድሚያ ሊታወቅ ይገባል፡፡

በተረፈ ሕዝቡ በተደጋጋሚ እንደሚጠይቀው ሀገሪቱ በአንድ ርዕዮተዓለም፣ በአንድ “መሪ ፓርቲ” የምትመራበት ጉዞ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማብቃት አለበት፡፡ አሁን እንደምናየው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአምባገነናችን ቀንበር የሚሸከምበት ጫንቃ የለውም:: የአንድ “አውራ ፓርቲነት”ና የበላይነትን ለማመቻቸት የተደነገጉት አፋኝ ህግጋትና እነርሱም ለማስፈፀም የተመሠረቱ ተቋማትም መፍረስ ይኖርባቸዋል፡፡

አገዛዙ ተግባራዊ አደርጋቸዋለሁ ያላቸው ለውጦች ካንገት ሳይሆን ካንጀት መሆኑን ለማረጋገጥም ከገዥው ኢህአዴግ የሚጠበቅ እጅግ ሰፊና አጣዳፊ ተግባራት አሉ፡፡

ይህ የአሁኑ የአገዛዙ መግለጫም ባለፉት ጊዜያት ሲሰጡ እንደነበሩ መግለጫዎች አማላይ ቃላት ብቻ ሆነው እንዳይቀሩ ከተፈለገ በዝርዝር የተቀመጠ ግልጽነት ያለው፣ በጊዜ ገደብ ላይ የተመሠረተ ተጨባጭ እርምጃ በአስቸኳይ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

በየቦታው በየተቋሞቹ ውስጥ በእስር ላይ የሚገኙትን የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ በነፃ ከመልቀቅ ጎን ለጎን የመላ ሀገሪቱን ሕዝብ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶችን ማክበርም ለነገ የማይባል የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ የሚታየው የማሰር፤ የማሳደድ፣ የመግደል፣ ወዘተ ተግባር አሁኑኑ መቆም አለበት፡፡

የመሰብሰብ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ፣ በሰላማዊ ሰልፍ የሚደረግ መብት....ወዘተ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ማክበር ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ቦታዎች የሚታዩ በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የሚደረገው ድብደባም ሆነ ወገኖቻችንን ማፈናቀል መቆም አለበት፣ እስካሁን በነበረው አሳሳቢ ሁኔታ ለተፈናቀሉም አስቸኳይና በቂ ድጋፍ መስጠት ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሀገር ጉዳይ ያገባናል ከሚሉ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ከሚንቀሳቀሱ የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች ግለሰቦችና ማህበረሰቦች፣ ጋር በሰለጠነ አኳኋን በጠረጴዛ ዙሪያ መወያየት ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው፡፡

የኛ ራዕይ በሀገራችን ውስጥ የግፍና የአድልዎ ሥርዓት አክትሞ፣ የሕግ የበላይነት ሰፍኖ፣ ሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተከብረው፣ የሁሉም ዜጎች የግልና የጋራ መብት ተረጋግጦ በሁሉም ባለድርሻዎች ሙሉ ተሳትፎ የዳበረ ሕገ-መንግስታዊ ሥርዓትን ዕውን ማድረግ ነው፡፡ ይህን ለማድረግም አሁን ከሰፈነው አምባገነናዊ አገዛዝ በመላቀቅ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ይቻል ዘንድ ሰላማዊ ሽግግር ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሽግግርም

ሰማያዊ ፓርቲ (ሰማያዊ)
BLUE PARTY (BLUE)

የችግሩ ዋና ምንጭ በሆነው በኢህአዴግ ብቻ ሊመራ አይችልም። ሁሉም ባለድርሻዎች የዚህ ሂደት ውጤት ባለቤት ሊሆኑ ይገባል።

በኛ እምነት የሀገራችንን ውስብስብ ችግሮች በመፍታት፣የሁሉንም ዜጎች አዎንታዊና ታዓማኒነትን ያገኘ ሥርዓት ለመመሥረት ያለው ብቸኛ አማራጭ በብሔራዊ መግባባትና በብሔራዊ እርቅ ጎዳና መጓዝ ብቻነው።

ይህ የብሔራዊ መግባባት መድረክ ከአግላይነት የተላቀቀ፣ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ያሳተፈ፣ የሁሉንም ድምፅ ለማድመጥ የተዘጋጀ፣ ለጋራ ችግሮቻችን የጋራ መፍትሔን ለመፈለግ የሚያስችል መሆን ይኖርበታል።ብሔራዊ እርቅና መግባባት ሲባል አገዛዙ ወይም የተወሰኑ ድርጅቶች ከደረሰባቸው ውጥረት ለመውጣት የሚጠቀሙበት የጊዜ መግዣ ታክቲክ ሳይሆን፣ በሀገራችን ውስጥ የሚታዩ ፖለቲካዊ፣ማህበራዊና ሌሎችንም ችግሮቻችንን ከቂም በቀል በፀዳ ሁኔታ ፊት ለፊት በጋራ መርምረን በእርቀ አሳቢነት፣ በብስለትና በመቻቻል፣ ስሜት አንድነቷ በተጠበቀ ኢትዮጵያ ሥር ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት የጋራ መፍትሄ ለመፈለግ የሚደረግ እውነተኛ ችግር ፈቺ መሆን አለበት።

በኛ በኩል ከላይ የጠቀስናቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚያሳትፍ ሂደትን ዕውን ለማድረግ ምንጊዜም ዝግጁ ነን። ብሔራዊ መግባባትና ዕርቅ እንዲሁም ኃላፊነት እወስዳለሁ ማለት ከአንገት በላይ ሳይሆን፣ቅንነት በተላበሰ ሁኔታ ከልባችን የምንፈፅመው ሲሆን ነው በሀገራችን ውስጥ የሚታየውና እያደገ የመጣው የፖለቲካ ቀውስ አዙሪት የሚሰብረው፣

ስለዚህ ኢህአዴግ በመላ አገሪቱ የታየው ሕዝባዊ እምቢተኝነትና ተቃውሞ አጣብቂኝ ውስጥ የከተተው መሆኑን በሚገባ ተገንዝቦና ራሱን ፈትሾ በእስከአሁኑ የአገዛዝ ዘመኑም የኢትዮጵያን ሕዝብ በብርቱ መበደሉን አምኖ የረፈደ ቢሆንም ሁሉም ዜጋ የአሁኑን ጅማሮ በመልካም ጎኑ የሚመለከተው ስለሆነ በአደባባይ እስረኞችን ለመፍታት የገባው ቃል በአስቸኳይ በተግባር አሳይቶ ለሌሎች ያልተፈቱ ችግሮቻችንንም ዙሪያ በጋራ ውይይት ለመፍታት በቅንንት መድረኩን ያመቻች ዘንድ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁን!!!**

**"ኢትዮጵያ በነፃነትና በክብር ለዘላለም ትኖራለች!"**

**ጥር 8 ቀን 2010 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**